የስድስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የሞዴል ፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

ቁጥር አምስት

1. ከሚከተሉት አንዱ የአፈር ሀብትን ለመጠበቅ ይረዳል

   ሀ) እርከን መስራት ለ) የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀም

   ሐ) አግድም ማረስ መ) ሁሉም

2. ማ ዕድናት በበህላዊ መንገድ በሚወጡበት ወቅት ምን ዓይነት ችግር ይፈጥራል?

   ሀ) የግብርና ምርት መጨመር ለ) የአየር ፀባይ መቀያየር

   ሐ) የመሬት አቀማመጥ መሻሻል መ) የዱር እንሣት ምቹ ቦታ ማግኘት

3. ሁሉም የተፈጥሮ ሃብቶች በሁሉም ቦያ እኩል የማይገኙበት ምክኛት ምንድን ነው ?

   ሀ) በሰዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ለ) የአየር ንብረት ከቦታ ቦታ መለያየት

   ሐ) በሃገር ገዥዎች ፍላጎት ስለሚሰራጩ መ) መልስ የለም

4. በሰሜንና በደቡብ ዋልታዎች አካባቢ የሚገኙ ቦታዎች የሙቀት መጠናቸው ለምን ዝቅተኛ ሆነ ?

   ሀ) ለምድር ወገብ ሩቅ ስለሆኑ ለ) የመሬት ገጽታቸው ከፍተኛ ስለሆነ

   ሐ) ለምድር ወገብ ያላቸው ርቀት ትንሽ ስለሆነ መ) ከፍተኛ ዝናብ ስለሚዘንብ

5. ከሚከተሉአ አንዱ ትክክል አይደለም

   ሀ) የቦታዎች ከፍታ ሲጨምር የሙቀት መጠን ይቀንሳለ

   ለ) ከምድር ወገብ ርቀው የሚገኙ ቦታዎች የፀሀይ ጨረር በሰያፍ ያርፍባቸዋል

   ሐ) ሞቃታማ የውቅያኖስ ሞገድ አካባቢው ሞቃት የአየር ንብረት እንዲኖረው ያደርጋል

   መ) ከባህር ጠረፍ ርቀው የሚገኙ ቦታዎች በቢጋን በከረምት አንድ አይነት የአየር ንብረት አላቸው

6. ከምስራቅ አፍሪካ ሃገሮች ከፍተኛ ቦታዎች የሚበዙባት ሀገር የትኛዋ ነች?

   ሀ) ሩዋንዳ ለ) ቡሩንዲ ሐ) ታንዛንያ መ) ማዳጋስካር

LIVEWORKSHEETS

7. ከታህሳስ እስከ የካቲት ወራት ዝናብ የሚያገኙ የምስራቅ አፍሪካ ሃገሮች የትኞቹ ናቸው ?

ሀ) ከምስራቅ አፍሪካ በሰሜን በኩል የሚገኙ ሀገሮች

ለ) ከምድር ወገብ በስተ ደቡብ የሚገኙ ሃገሮች

ሐ) በምድር ወገብ አካባቢ የሚገኙ ሃገሮች

መ) መልስ የለም

8. የደም ህዋስ የሆነው የትኛው ነው

ሀ)ቀይ የደም ህዋስ ለ)ነጭ የደም ህዋስ

ሐ) ፕሌትሌት መ) ሁሉም

9. ከሚከተሉት አንዱ ድንጋይን ከመሬት ለመፈንቀል ይረዳል

ሀ) መፈንቅል ለ) ሽብልቅ ሐ) ሽክርክሪት መ) በክራ

10. በቀላሉ ሊታደስ (ሊተካ) የሚችለው የጉልበት አይነት የትኛው ነው ?

ሀ) የመኪና ባትሪ ለ) የሰዓት ድንጋይ

ሐ) የባትሪ ድንጋይ መ) ውሃ

11. **ንጥረትን** የምንጠቀመው ምን ዓይነት ቁሶች ሲቀላቀሉ ነው ?

ሀ) ፈሳሽ እና በፈሳሹ የማይሟሟ ጠጣር

ለ) ሁለት የማይሟሙ ጠጣሮች ሲቀላቀሉ

ሐ) እፍግታቸው ተመሳሳይ እና የሚዋሃዱ ፈሳሾች ሲቀላቀሉ

መ) እፍግታቸው የተለያየ ፈሳሾች ሲቀላቀሉ

12. ..... ማለት የውሃ ትነት ወደላይ በመውጣትና በመቀዝቀዝ ተመልሶ ወደመሬት

የሚወርድ እርጥበት ነው ::

ሀ) ደመና ለ) ነፋስ ሐ) ዝናብ መ) ሙቀት

13. ጥቃቅን ቀዳዳዎች ባሉት እቃ ድብልቆችን የምንለይበት ዘዴ

ሀ) ቀረራ ለ) ጥሊያ ሐ) ትነት መ) ንጥረት

LIVEWORKSHEETS

14. የድብልቅ ይዘቶች በአይን የሚታዩ ከሆነ ድብልቁ ምን ተብሎ ይጠራል ?

ሀ) ልዩ ዘር ድብልቅ ለ) ዋህድ ዘር ድብልቅ

ሐ) ውህድ መ) ልዩ ቁስ

15. የድብልቅ ምንዝሮች የማይለዩበት ምክንያት ምንድን ነው ?

ሀ) ምንዝሮች የተቀላቀሉት በኬሚካላዊ መንገድ ስለሆነ

ለ) ምንዝሮችን በአይናችን ማየት ስለምንችል

ሐ) ምንዝሮች የተቀላቀሉት በአካላዊ መንገድ ስለሆነ

መ) መልስ የለም

16. አንድን ስራ የማስላት አቅም (ችሎታ) ..... ይባላል

ሀ) ሙቀት ለ) ጉልበት ሐ) ብርሃን መ) ሃይል

17. ከአለቶች ስብስርባሪ ከዕፀዋት እና ከእንሥት ብስባሽ የሚፈጠር የመሬት የላይኛው ክፍል ምን ይባላል?

ሀ) አፈር ለ) አለት ሐ) ድንጋይ መ) ተፈጥሮ

18. ከሚከተሉት አንዱ የተፈጥሮ ክስተት አይደለም

ሀ) ቀን እና ሌሊት ለ) የመሬት መንሸራተት

ሐ) እንስሣት መ) የወቅቶች መፈራረቅ

19. የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም ጠቀሜታው ምንድን ነው ?

ሀ) የአፈሩን አሲድነት ይጨምራል ለ) አፈሩ እንዲሸረሸር ያደርጋል

ሐ) የግብርና ምርቶችን ይቀንሳል መ) የአፈሩን ለምነት ይጨምራል

20. ባዶ ወይም ደን በሌለበት ቦታ ዛፎችን እና ችግኞችን መትከል ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ) ድነና ለ) ችግኝ ተከላ ሐ) ዳግም ድነና መ) መልስ የለም

21. የአፈር መሸርሸር ምክንያት ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው ?

ሀ) የመሬት አቀማመጥ ለ) የአፈሩ አይነት

ሐ) የእፅዋት ሽፋን ምምናመን መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

22. ከሚከተሉት አንዱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የአፈር አይነት ነው ::

ሀ_ ሲቶሶል ለ) በርቲሶል ሐ) ፈራሶል መ) አክሪሶል

23. ከሚከተሉአ አንዱ የሽግግር ቀጠና በመባል ይታወቃል::

ሀ) የበረሃ የአየር ንብረት ለ) የደጋ የአየር ንብረት

ሐ) የሳር ምድር ሞቃታማ የአየር ንብረት መ) የሃሩር ሞቃታማ የአየር ንብረት

24. አንድ አካባቢ በረሃ ነው ብሎ ለመጥራት የዝናብ መጠኑ (አመታዊ አማካይ) ስንት መሆን አለበት?

ሀ) ከ 250 ሚሜ በታች ለ) ከ250 ሚሜ በላይ

ሐ) ከ600 ሚሜ በላይ መ) የዝናብ መጠኑን ማወቅ አይቻልም

25. ለግብርና ስራ በቂ ዝናብ የሚያገኙ የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የትኞቹ ናቸው ?

ሀ) ታንዛን ያ ለ) ዩጋንዳ ሐ) ሩዋንዳ መ) ሁሉም

26. ጠንካራ የሆኑ ነገሮችን ለመሰርሰር እና ነገሮችን አጥብቆ ለማሰር የሚረዳን የትኛው ነው ?

ሀ) ሽብልቅ ለ) ሽክርክሪትና ዘንግ ሐ) መፍቻ መ) መፈንቅል

27. ቀላል መኪናዎችን ለምን እንጠቀማለን ?

ሀ) ጊዜን ለማባከን ለ) ትንሽ ስራን በረጅም ጊዜ ለመጨረስ

ሐ) ጉልበትን ለመቆጠብ መ) ጉልበታችንን ለመፈተን

28. ከሚከተሉት አንዱ የአየር ንብረት መገለጫ አይደለም

ሀ) በቦታው አቀማመጥ የተነሳ የተለያየ የአየር ንብረት ይኖራል

ለ) የአየር ንብረት ይዘቶች መጠን በሰአታት እና በቀናት ይለያያል

ሐ) የአየር ንብረት ይዘቶች ለአመታት መጠናቸው አይለያይም

መ) መልስ የለም

29. በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ብቻ የሚገኘው የአየር ንብረት ክልል የትኛው ነው ?

ሀ) የሐሩር ሞቃታማ የባህር ዳርቻዎች ለ) የሳር ምድር ሞቃታማ የአየር ንብረት ክልል

ሐ) የደጋ የአየር ንብረት ክልል መ) የበረሃ የአየር ንብረት ክልል

LIVEWORKSHEETS

30. ሚሚውን እና አሚሚውን ለመለየት የምንጠቀምበት የድብልቅ መላያ ዘዴ የቱ ነው ?

ሀ) ንጥረት ለ) ትነት ሐ) ጥሊያ መ) ሀ እና ለ

31. አንድን ነገር በሁለት ለመክፈል የሚረዳ ቀላል መሳሪያ ....

ሀ) ዘንባይ ወለል ለ) ሽብልቅ ሐ) መፈንቅል መ) መፍቻ

32. በመሬት ላይ የሙቀት፣የንፋስ፣የዝናብ እና አየር ግፊት ስርጭት እኩል እንዳይሆን የሚያደርጉ ተፈጥሯዊ

ምክንያቶች ምን ይባላሉ ?

ሀ) የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ሐ) የደጋ የአየር ንብረት

ለ) የሐሩር የአየር ንብረት መ) የበረሀ የአየር ንብረት

33. በመጠናቸው በጣም ቲኒኒሽ የሆኑከብ ቅርጽ ያላቸው ሰውነታችን ሲደማ ብዙ ደም እንዳይፈስ ለማርጋት ይጠቅማሉ

ሀ) ነጭ የደም ህዋስ ሐ) ፕሌትሌቶች

ለ) ቀይ የደም ህዋስ መ) ሁሉም

34. የልብ ትርታን የምናዳምጥበት መሳሪያ .... ተብሎ ይጠራል

ሀ) ቴሌስኮፕ ለ) ማይክሮስኮፕ ሐ) ስቴቶስኮፕ መ) መ/የለም

35. ከሚከተሉት ልዩ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) የደረት መስፋት ሐ) የዳሌ መስፋት

ለ) የድምጽ መጎርነን መ) በፊት ላይ ጸጉር ማብቀል

36. .... ማለት አክሲጅን ወደ ሰውነታችን ውስጥ የማስገባትና ካርበንዳይ አክሳይድን ወደ ውጭ የማስወጣት ሂደት ነው

ሀ) ሥራዓተ ልመት **ለ) ትንፈሳ** ሐ) የልብ ምት መ) ትርታ

LIVEWORKSHEETS

37. ከሚከተሉት አንዱ ውኃና አልሚ ምግብን የሚይዝ የደም ክፍል ነው

ሀ) ደም ለ) የደም ህዋስ ሐ) የደም ዑደት መ) ፕላዝማ

38. ከሚከተሉት አንዱ ከደም ስር ዓይነቶች ውስጥ አይደለም

ሀ) ቀይ የደም ህዋስ ለ) ደም ቅዳ ሐ) ደም መልስ መ) ሁሉም

39. ..... በየ 28 ቀናት በማህፀን በዕንቁልጢ ውስጥ የሚካሄድ ተፈጥሯዊ ክስተት ነው

ሀ) ኮረዳነት ለ) የወር አበባ ሐ) ጉርምስና መ) ሀ እና ለ

40. በሳንባ ውስጥ የሚካሄድ የአየር ልውውጥ ምን ይባላል ?

ሀ) ትንፋሽ ለ) ትንፈሳ ሐ) ሳንባ መ) የሳናንባ ዑደት

LIVEWORKSHEETS